# የዘጋ ባህታዊ የሚያድነው እራሱን ብቻ ነው።

ከበልጀግ አሊ

ከአንድ ወድ ጓደኛዬ ጋር ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የሳምንቱን ማለቂያ በጭውውት ልናሳልፍ ተቃጥረን ነበርና በዚያውም ደግሞ በሰሞኑ በፓልቶክ ሱሳችንን ለመወጣት ፤ምን ይኖር ብለን መመዝገብ ጀመርኩ ። ከወትሮው በተለየ አዲስ የሆን ፣ ለሌሎች ላይሆን ይሆናል፤ ግን ለኔ አዲስ የሆነ ክፍል አገኘሁ ። ብዙም አልወሰደብኝ የበሰለ ውይይት እንደሚደረግ ለማወቅ ቻልኩ ። ከተሳዳቢዎቹ ሁኔታም የአዲሱ ከፍል አጋፈሪዎች አፍቃሪ ኢሕአፓ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ከሌላ ከፍል የሚመጡ ሰርጎ ገቦች ተፃፈልን።

በጣም የተደሰኩበት ነገር ቢኖር ግን አጋፋሪዎቹ ይህንን አለመካዳቸውና በኢሕአፓነታቸው መኩራታቸውንን ነበር ሲገልፁ የዋሉት ። እንዲያውም ሊሰድቡዎቸው የመጡትን ሁሉ በየተራ እያረጋጉ በጥሩ ሁኔታ ውይይቱ ቀጠለ። ምንም እንኳን ስድቡ ቢቀጥልም በጣም የሚያስደስተው ተሳዳቢዎቹ ሳይቀሩ የአጋፋሪዎቹን ችሎታ ማክበራቸው አልቀረም ።

የዛሬ ፅሁፌ ከፓል ቶኩ ጋር ይያያዝ እንጂ ዋናው አላማዬ ኢሕአፓና አባላቶቹ ከአሁን በሁዋላ በግለ ሰብም ሆን ወይም በድርጀት መልክ ተደራጅተው የሚሳደቡትን ለተቃወሚዎች ህብረት ሲሉ ማለፍ እንደሌለባቸው ይሰማኛል ። በዚህ ጨዋታ ወስጥ መግባት ደግም ሃይልን ሊያዳክም እንደሚችልም ጥርጥር የለኝም ። ቁም ነገሩ ግን ታሪኩን በቅጡ ለማያውቁት ወይም ላላነበቡት የተጀመረው በውሸት የማጥላላት ዘመቻና የወያኔ አንቀላፊዎች ቅስቀሳ ስንቱን አገሩን የሚወድ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ሊያወናብድ እንደሚችልና ፀረ ኢሕአፓ ሊያደርጋቸው መቻሉን መዘንጋት የለበትም።

የምንጠየቀው ለሰራነው ብቻ ሳይሆን ልንሰራው ስንችል ላልሰራነውም ጭመር ነው ። እንደ ባህታዊው ዘግተን የራሳችንን አቋም ጥርት አድርገን ብንቀመጥ መንግስተ ሰማያት የኛ ላትሆን ትችላለች ። እግዝሀብሔር ስለኔ ምን አስተማርክ፣ ምን ብለህስ መሰከርክልኝ ብሎ መጠየቁ ስለማይቀር መልሳችን አጥጋቢ እንዲሆን መዘጋጀት ከአሁኑ ያስፈልጋል ። ሁኔታው በጣም ማሳሰቡ አልቀረም። አንዳንድ ንፁህ ኢትዮጵያውያን ፣ ኢትዬጵያን ለማጥፋት በገፍ ገንዘብ እያዋጡ መሆናቸውን መረዳት አለብን ።

በዚህች ምሽት ትንሽ ሰዓታት የፓልቶክ ውይይት ላይ ልንገነዘበው የቻልኩት ያ የታመቀ የኢሕአፓ የማስተባበር፣ የማስተማር ፣ የማሰገንዘብ ፣ ችሎታና ባህል የተካፋዮቹን ቀልብ ሊስብ መቻሉ ሲሆን ይኸ የተከመረ ችሎታ (ፖቴንሺአል) አሁን አገራችን በገባችበት አጣብቂኝ መደረግ ስላለበት ወቅታዊና አሰፈላጊ ውይይት በጣም አስፈላጊ ነው ።

ለኔም ሆነ ለሌሎቹ ግልፅ ሆኖ የሚታየኝ ኢሕአፓ በፓርቲነቱ እራሱን የሚገልፅባቸው መንገዶች ሁሉ ሊከፈቱ ይገባል እላለሁ።በዚህ መንገድ ብቻ ነው ወቅቱ የሚጠብቅብን መወጣት የምንችለው። እራሳችንን ማፅዳትና ጥራት ያለው አቋም መያዝ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ከምንጠብቀው ድል በቅርብ አያደርሰንም ።

**በልጀግ አሊ**